# የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ

ኢየሱስም  አንዲህ አላቸው የህይወት አንጀራ አኔ ነኝ ወደ አኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በአኔ የሚያምንም ከቶ አይጠማም (ዮሐ 6፡35)

የህይወት አንጀራ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን

Bread of Life International Church

**መጠሪያ ስም**

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በመባል የምትጠራው በምዕራብ ለንደን የህይወት እንጀራ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ናት፤፤

ዓርማ ፡-

ትርጉም &-

1. **የተገለጠው መጽሐፍ** ፡- የቤተክርስቲያኒቷ መሰረተ እምነት የተገነባው 66ቱን መጽሐፍ የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ እና በሙሉ ስልጣን የምትታዘዘውም እርሱን እንደሆነ ያመለክታል፤፤ ዘዳ 6፤-7-8 2ጢሞ 3፡ 17

2. **እሳት ፤-** እሳት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጠበት መገለጫው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን እሱም መለኮታዊ እንደሆነና በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ አድሮ እንደሚረዳቸው እንደሚያጽናናቸው እና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ ከአብ ና ወልድ እኩል መለኮት የሆነ እንዲሁም ክርስቶስን የሚያከብር ነው ፤ ዮሐ 14፡ 16 ፣ 16፤ 13 ማቴ3፤16

- በተጨማሪም አማኞችን በእሳት እንደሚያጠምቃቸው እና ሐይል እንደሚሰጣቸው ያመለክታል፤ የሐዋ 1፡8

3. **መስቀል**፤- መስቀል መገለጫው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ የተላከ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማሪያም የተወለደ የሰው ልጆችን ኃጢአት ሁሉ በመስቀል ተሸክሞ የተሰቀለ የሞተ የተቀበረ በመጨረሻም ከሙታን ተነስቶ ወደ አብ ያረገ በዳግም ምጻት ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ስለእኛ በአብ ፊት የሚታይ መሆኑን ያመለክታል የቤተክርስቲያንም እምነት የተመሰረተው በዚሁ ላይ ነው ፤፤ 1ቆሮ 1፡ 18 ፣ 15፤13 ሉቃ፤ 24፡ 51

4 **ዓለም** ፤- አለም የተፈጠረው በእግዚአብሔር ቃል እንደሆነና ተደግፎ የቆመውም በዚሁ እንደሆነ ያመለክታል እንዲሁም ወንጌል ለአለም ሁሉ መሰበክ ያለበት ብቸኛው እውነት እንደሆነ የሚያመለክትም ነው ዕብ 1፤3 ፣ ማቴAa 28፤ 18-20

- ዓለም በሀገር የተከፋፈለና ልዩ ልዩ የሰው ዘር ይኖርበታል በቋንቋ እና በነገድም የተከፋፈለ ነው ነገር ግን ለሁም የሚሆንና ሁሉም በአንድነት የሚያገናኘው አልፎም አንድ የሚደርገው ወንጌል ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰበክ ጌታ ታላቅ ትእዛዝን ለተከታዮቹ ሰጥቷል፤

**የእምነት መግለጫ**

- ❖ **የእምነት መግለጫ ማለት ቤተክርስቲያን በግልም ሆነ በወል እምነቷ የተመሰረተው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ላይ ነው ማለት ነው ፤፤**

1. ስድሳ ስድስቱን የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ምንም ስህተት የማይገኝበት እምነትንና ተግባርን በሚመለከት የመጨረሻው ስልጣን ያለው እንደሆነ እናምናለን
2. በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር ወልድ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአካል ሶስት በመለኮት አንድነት ዘላለማዊ አምላክ እናምናለን
3. አለማትን ካለመኖር ወደ መኖር ባመጣ በእግዚአብሔር ፍጹም ስልጣን እናምናለን

4. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ የተላከ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማሪያም መጸነሱን እና መወለዱን ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ለሰው ልጆች ቤዛ በመሆን በመስቀል ላይ መሞቱን መቀበሩን በሶስተኛው ቀን ከሞት መነሳቱን ለአርባ ቀን ያህል መታየቱን ከዚያም ወደ አብ ማረጉን አሁን በአብ ቀኝ ሆኖ ስለእኛ መማለዱን በመጨረሻም በህያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ በክብር እንደሚመለስ እናምናለን
5. መንፈስ ቅዱስ እነደ አብና ወልድ ሁሉ የመለኮት ባህሪያት ሁሉ ያሉትና ፍጹም አምላክ እንደሆነ እናምናለን
6. መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ጥቅምና አገልግሎት እንዲሁም መታነጽ በኤፌ 4 ፤11 ላይ እንደተገለጸው ሐዋርያትን፤ ነብያትን ፤ወንጌል ሰባኪዎችን፤ መጋቢዎችን(እረኞችን)፤አስተማሪዎችን እንዲሁም ሌሎች የአገልግሎት ስጦታዎችን እንደሚሰጥ እናምናለን
7. በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዱ ሁሉ በሚገኙበት የክርስቶስ አካል በሆነና በአንዲት ቤተክርስቲያን እናምናለን
8. ሰውነትን በሚሸፍን የአንድ ጊዜ የውሀ ጥምቀት በተጠያቂነት ደረጃ ላይ ላለ ጌታን እንደ ግል አዳኙና ጌታው አድርጎ ለተቀበለ እና ለተከተለ ሁሉ ክርስቶስ እንደተነሳ በትንሳኤ ከሞት እንደሚነሳ የሚገልጥበት መንገድ ስለሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም መደረግ ያለበት እንደሆነ እናምናለን
9. ሰው ወንድ ወይም ሴት ሆኖ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ከቡር ፍጡር እንደሆነ እናምናለን
10. ሰው በሀጢአት መውደቁን ከዚህም የተነሳ የእግዚአብሄር ቁታና ፍርድ ያለበት በደለኛ እንደሆነና ከዚህም ፍርድ ሊድን የሚችለው የዘላለም የኃጢአት ቤዛ የሆነውን ክርስቶስን ሲቀበል እንደሆነ እናምናለን
11. ጋብቻ እድሜአቸው ለአቅመ አዳምና ሄዋን የደረሰ ወንድና ሴት ብቻ መካከል የሚደረግ ቅዱስ ስርዓት እንደሆነ እናምናለን
12. በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዱ ሁሉ በሚገኙባት የክርስቶስ አካል በሆነች በበአኒዲት ቅድስት ቤተክርስቲን እናምናለን
13. በሙታን ትንሳኤ በኃጥአን ላይ በሚደርሰው የዘላለም ፍርድና አማኞች በሚቀበሉት የዘላለም ህይወት እናምናለን

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ዓላማ ተግባርና ስልጣን

### ዓላማ

1.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን የሰጠውን ታላቁን ተልዕኮ የምስራቹን ቃል ለፍጥረት ሁሉ በመስበክ በማስተማር ደቀመዝሙር ማድረግ (ማር 16፤ 15 ሮሜ 10፤4)

2. እንደ አንድ ህዝብ በጌታ ፊት በወንድማማች መዋደድ ለእርስ በርስ በዋደድና በመተናነጽ በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ምሳሌ በመሆን ሰውን ሁሉ በክርስቶስ ማወቅና ማገልገል

3. ምእመናንን በመንፈሳዊ ህይወታቸው ማሳደግ የየአከባቢ ህብረቶች መመስረት የተመሰረቱትንም ማደራጀትና በማሳደግ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ማድረስ

4. የቤተክርስቲያንን አንድነትና መሰረተ እምነት ተጠብቆ እንዲኖር ማድረግ

### ተልዕኮ

- ✓ ክርስቶስን ያማከለ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ መሰረት ያደረገ እና መንፈስ ቅዱስን ሐይል ያደረገ አገልግሎት በቤተክርስቲያን ማድረግ

- ✓ አጋጣሚውን ሁሉ በመጠቀም ወንጌልን ከምዕራብ ለንደን በመነሳት በሁሉም የለንደንና የዩኬ አከባቢዎች እንዲሁም በአለም ሁሉ ማድረስ
- ✓ በአማርኛ ቋንቋ በለንደን የአገልጋዮች የመጽሐፍ ቅዱስ የስልጠና ማዕከል በሰርተፍኬትና ዲፕሎማ ፕሮግራም ተቋም ማቋቋም

**የቤተክርስቲያን ተግባር**

የቤተክርስቲያን ተግባር ባጭሩ ሲገለጽ እግዚአብሔርን ማምለክ እርስበርስ መተናነጽ ወንጌልን ላልሰሙት ማሰራጨት እንዲሁም የርህራሄ አገልግሎት ነው ከዚሁ ጎን ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ በመስማት ሁል ጊዜ ጌታ እንደረዳት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈለግ የሚከተሉትን ለማድረግ ከጌታ የተደነገገላት ስልጣን አላት

1. በታመሙት ላይ እጅ በመጫን ጌታ እንዲፈውሳቸው ጸሎት ማድረግ
2. ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥሪ ያላቸውን አገልጋች መንፈስ ቅዱስን በመስማትና በመለየት ፍሬአቸውንም በማየትና በመመዘን በኤፌ 4፣11 ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን በሰጠው መሰረት በሐዋርያነት በነብይነት በወንጌላዊነት በእረኝነት እንዲሁም በአስተማሪነት ጸጋ ያላቸውን እንደየስጦታቸው እውቅና በመስጠት እንዲያገለግሉ ማድረግ
3. ሽማግሌዎችንና ዲያቆናትን መሾም
4. ቅድስናን በሚያጎድፍ ተግባር በተገኘ አገልጋይም ሆነ አባል ላይ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ
5. በቤተክርስቲያን የተደነገጉትን ቅዱስ ስርዓት እንደ የጌታ ራትና ጥምቀት ማከናወን
6. ልዩልዩ ስርዓቶች እንደ ጋብቻ ቀብር ልጆችን ለጌታ አሳልፎ የመስጠት አገልግሎት ማከናወን

**እሴቶቻችን**

እሴቶቻችን በህይወታችን በግልና በህብረት እንዲሁም በልዩ ልዩ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ላሉ የቤተክርስቲያን አማኞች ሁሉ አንድ ወጥ የሆነ መንፈሳዊ የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖረን ከማስቻሉም ባሻገር የእግዚአብሔርን ቃል መሰረት ያደረገ መንፈሳዊ አቋም መያዝ እንድንችልም የሚረዳ ነው ፤፤

1. **ቅድስና**

ቅድስና ለእግዚአብሔር የመለየታችን ምልክት ነው ያለ ቅድስናም እግዚአብሔርን ማስደሰትም ሆነ ማየት

ስለማይቻል በቃልና በተግባር በሀሳብና በድርጊት በጽድቅ መኖር፤፤

2. **እግዚአብሔርን ማክበር**

   እግዚአብሔርን ማክበር በሁሉ ነገር እርሱን ማስቀደም ሲሆን በመታዘዝ መልካም ምስክርነት ያለውን ህይወት መኖር
3. **ፍቅር**
   - ✓ የፍቅር መለኪያውና ሚዛኑ ክርስቶስ ስለእና የከፈለው ዋጋ እንደሆነ ተረድተን ሰውን ሁሉ ያለ ዘር ቀለም አና ቋንቋ ልዩነት አኩል መውደድ ( 1ቆሮ 13 1-3)

- ✓ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታልፎ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ለደቀመዛሙርት ከሰጣቸው ቁልፍ የህይወት መመሪያዎች አንዱ ሰዎች በፍቅራሁ ይወቁዋችሁ የሚል ነው (ዮሐ13 ፤35)
- ✓ የእግዚአብሔር ቃል እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም እዳ አይኑርባችሁ / ሮሜ 13፤8/ ስለሚል ቤተክርስቲያን ከፍቅር በላይ ምንም ሊኖር አይችልም

**4. ደቀ መዝሙርነት**

የክርስቶስ ፍጹም ተከታይ በመሆን የህይወታችንም መሪና ባለቤት አርሱ እንደሆነ በመገንዘብ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ህይወት መኖር

ጌታ የጠራን ደቀመዝሙር እንድንሆንና ወደ እርሱ የመጡትን እያስተማርን እኛም ደቀመዝሙር እንድናደርግ ነው (ማቴ 28 18- 20)

**5. ታማኝነት**

- ➢ ለጌታ ብቻ በእውነትና በታማኝነት እለት እለት በሰውና በእጊዚአብሔር ፊት ተመሳሳ ህይወት መኖር
- ➢ በኑሮአችን በስራችን እንዲሁም በቤተክርስቲያን ባለን አገልግሎት ታማኝ መሆነ
- ➢ እግዚአብሔር በሰጠን በገንዘባችን ለጌታ ሚገባውን እየሰጠን መኖር
- ➢ በትዳራችንና ከሰው ሁሉ ጋር ባለን ግንኙነት ታማኝ መሆን

**6. ጾምና ጸሎት**

- ➢ ጾምና ጸሎት የቀደመችው መጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እሴት እንደሆነ በመረዳት በዚህ ክፉና በወደቀው ዓለም እንዴት መኖር እንድንችል የሚረዳንን ጸጋ ለማግኘት መጾም መጸለይ
- ➢ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ጾምና ጸሎት መታወቂያቸው እንደሆነ ሁሉ የዘመናት የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምሳሌ እንድትሆን ያስቻላትን ጾምና ጸሎት መተግበር (ሐዋ 13፤13)

**7. ግልጽነት**

- ➢ በእግዚአብሔር ዐይኖች ፊት ሁሉም ነገር የተራቆተና የተገለጠ እንደሆነ በመገንዘብ በቤተክርስቲያን ለሚታቀደውም ሆነ የሚደረገውን ለምእመናን በግልጽ ማድረግ እና ባለመሰወር ማሳወቅ
- ➢ አማኞች በግልም ሆነ በጋራ ማንኛውንም ነገር በቤተክርስቲያን የሚደረገውን የማወቅ መብት ስላላቸው ከአባላት የተደበቀ ነገር የለም

**የቤተክርስቲያን አባልነት**

የቤተክርስቲናን አባል ማለት በቤተክርስቲያን የአባላት መመዝገቢያ ቅጽ ተመዝግቦ ያለ ወይም የቤተክርስቲያንን ምሰረተ እምነት ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ አብሮ በተባባሪነት የሚያመልክ እና የሚያገለግል ማለት ነው

1. ክርስቶስን እንደግል አዳኙ እና ጌታው አድርጎ የተቀበለና መሰረታዊ የክርስትና ትምህርት ተምሮ የውሃ ጥምቀት በመውሰድ ወደ ህብረት የተቀላቀለ

2. ከሌላ ሀገራ ወይም ከተማ መሰል ከሆነች አጥቢያ ህብረትና ቤተክርስቲያን መሸኛ ይዞ የመጣ/ች/ ካልተቻለም የቤተክርስቲያኒቱን መሰረተ እምነት አምኖ/ና የተቀበለ/ች እና አባል ለመሆን ፍቃደኛ የሆነ/ች

**የቤተክርስቲያን መዋቅር**


- የቤተክርስቲያን መዋቅር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያቅፍ ይሆናል፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. የመሪዎች ስብስብ
3. መጋቢዎች
4. አስተማሪዎች
5. ወንጌላውያን
6. ዲያቆናት
7. የአገልግሎት ዘርፍ
8. ኢቃቤ ንዋይ /ገንዘብ ያዥ/
9. የሂሳብ መርማሪ / ኦዲተር/

**የቤተክርስቲያን አስተዳደር**

- ቤተክርስቲያን በአዲስ ኪዳን እንዳለችው እንደ መጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር የምታምንና የምትከተል ሲሆን ይህም የቤተክርስቲያን አመራር በአንድ ግለሰብ ሳይሆን ፕሪስቢቴሪያን / የብዙሃን ሽማግሌዎች አስተዳደር ዘይቤ/ ይሆናል ፡፡ ይህም አስተዳደር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆኑ አንጻር በቤተክርስቲን ለሚወሰኑ ማንኛውም ውሳኔዎች በጋራ በመሆናቸው የብዙሃን ሀሳብ የተንሸራሸረበት ስለሚሆን ለስህተት እንዳይዳረግ ያስችላል
- በዚህም መሰረት መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ጥቅምና መታነጽ የሚሰጣቸው የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ የቤተክርስቲያን የመሪዎች አካል እንደሆኑ ቤተክርስቲያን ብታምንም አሁን ባላት ነባራዊ ሁኔታ ግን አስተዳደራዊ መዋቅሯ በመጋቢና በሽማግሌዎች በጋራ የምትመራ ይሆናል ፡፡
- ቤተክርስቲያን በብዙሃን ሽማግሌዎች መመራቷ የቤተክርስቲንን መንፈሳዊነት ከማስጠበቁም ባሻገር ሚዛናዊ አስተዳደር እንዲኖራትም ያስችላታል ፤

# የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ አገልግሎት መዋቅር



**አጠቃላይ ጉባኤ**

**ትርጉም ፤-** የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላትን ሁሉ ያካተተ የምእመናን ጉባኤ ነው

**አጠቃላይ ጉባኤ ተግባር**

2. የቤተክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ይሰጣል በተስማማበትም መሰረት ያጸድቃል
3. በቤተክርስቲያን በሚቀርበው የአገልግሎትም ሆነ የፋይናንስ ሪፖርት ይሰማል ግልጽ ባለሆነለት ጉዳይ ይጠይቃል
4. የቤተክርስቲያንን አንድነትና ህብረት መጠበቅ
5. ማንኛውንም ገንቢ ሀሳብ ለቤተክርስቲያን መሪዎች መለገስ
6. ጉባኤው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል እንደአስፈላጊነቱም ሌላ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል ይችላል

**ሽማግሌዎች**

ሽማግሌዎች ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ተመርጠው ቤተክርስቲያንን እስከ ተመረጡበት ዓመት ያህል በአስተዳደርና የክርስቶስን ቤተክርስቲያን በታማኝነት በመጠበቅና ምእመናንን ከማናቸውም ስህተት በመጠበቅ በእረኝነት የሚያገለግሉ ናቸው ሐዋ 20፤28

**የሽማግሌዎች አወካከል**

በቲቶ 1-5-6 ; በ1ኛ ጢሞ3፡2 5፡17 መሰረት አዲስ ሽማግሌዎችን ለመምረጥ ወይም ለመሾም ሲያስፈልግ ነባር ሽማግሌዎች በአገልግሎት ዘመናቸው ከተከተ አሊያም ከምእመናን መካከል የመሪነት ስጦታ መንፈስ ቅዱስ የሰጣቸውን በጸሎት በመለየት ለአባላት ስማቸው ከተነገረ ቦኋላ በሁለት ሳምንታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በምዕመናን ፊት በቀደሙት ሽማግሌዎችና መጋቢዎች እጅ በመጫን ለቀጣይ አገልግሎታቸው ይጸለይላቸዋል

**የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች አገልግሎት**

1. የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን መንፈሳዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍና በመመራት በበላይነት ይመራሉ
2. የቤተክርስቲንን የወደፊት እቅድ ያወጣሉ ከየአገልግሎት ክፍሎች ጋር በመሆን እና በመመካከር አዳዲስ ራእይ ይተልማሉ
3. በተለያየ ጊዜ ከጌታ ለአገልግሎት ጥሪ ያላቸውን አገልጋዮች ከቤተክርስቲያኒቱ ነባር አባላትና የዘርፍ መሪዎች ጋር በመመካከር ለአገልግሎት በጸሎት ይለያሉ ያስማራሉ
4. የእግዚአብሔር ቃል በትክክና በንጹህ መንገድ መቅረቡን ይከታተላሉ ምእመናንን ከሀሰት ትምህርት ይጠብቃሉ ያስተምራሉ ይመክራሉ ይጎበኛሉ ያጽናናሉ አልፎም በቤተክርስቲያን ውስጥ የስነምግባር ችግር የታየባቸውንና ያላቸውን አባላት ይገስጻሉ፤ አልፎም የእርምት እርምጃም ይወስዳሉ
5. ማንኛውንም የሰው ሐይል ቅጥር በተመለከተ ማስታወቂያ በማውጣትም ሆነ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ረገድ ይሰራሉ
6. የስራ መደብ ዝርዝር ያዘጋጃሉ የስራተኛውንም የስራ አፈጻጸም ይከታተላሉ ይገመግማሉም
7. በየአራት ወሩ የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ በተመለከተ ከአገልግሎት ዘርፍ መሪዎች ጋር በመሆን ይመካከራሉ ስራቸውንም ይገመግማሉ ተጨማሪ ገንቢ ሀሳብም ከዘርፍ መሪዎች ይወስዳሉ በተጨማሪ ከአጠቃላይ ጉባኤ ጋር በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋሉ

8. የቤተክርስቲያንን የሂሳብ መርማሪዎች ወይም ኦዲተሮች ይሾማሉ
9. የቤተክርስቲያኒቱ ትረስቲስ ወይም ዳይሬክተር በመሆን ያገለግላሉ

**የሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን**

1. የሽምግልና አገልግሎት እጅግ አድካሚና ብዙ ጊዜን ከመጠየቁ አንጻር የአገልግሎት ዘመኑ ሶስት አመት ሲሆን ለተጨማሪ ሶስት ዓመት በአገልግሎቱ ፍሬአማ ከሆነና ቤተክርስቲያን አገልግሎቱን ፈልጋ ከተመረጠ እንደገና ማገልገል ይችላል ከዚህ በኋላ ግን እንደገና ለማገልገል ቢያንስ ለአንድ ዙር ማረፍ ይኖርበታል
2. የአገልግሎት ዘመኑን ሳይጨርስ በሚለቅ ሽማግሌ ምትክ የሚመረጥ ሲሆን እንደሌሎቹ ሁሉ አገልግሎቱ እስከ ቀጣዩ የሽምግልና አገልግሎት ዘመን ድረስ ይሆናል

**የመሪዎች ስብስብ ስርዓት**

የመሪዎች ስብስብ የራሱ የሆነ የውስጥ ደንብ ይኖሩታል በውስጥ ደንቡም መሰረት ሰብሳቢ ም/ ሰብሳቢ ጸሐፊና የሂሳብ ሹም ይመርጣል ውጤቱንም ለአጠቃላይ ጉባኤ ያሳውቃል፤፤

**የመሪዎች ስብስብ ሰብሳቢ አገልግሎት**

በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው ማንኛውም እንቅስቃሴ በሰብሳቢነት ይመራል ከጸሐፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎች ያዘጋጃል ስብሰባን በሰብሳቢነት ይመራል

**የመሪዎች ስብስብ ጸሐፊ**

1. ለቤተክርስቲያን ለሚላኩ ደብዳቤዎች በወቅቱ ምላሽ ይሰጣል
2. በቤተክርስቲያን ለሚደረጉ ክንውኖች ሪፖርት ያዘጋጃል
3. በስብሰባዎች ሁሉ ላይ ቃለ ጉባኤ ያዘጋጃል

**ዲያቆናት ፡-** በ1ኛ ጢሞ 3፡9 -10 ቲቶ 2፡ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ እንዳስቀመጠው ልክ እንደ ሽማግልዎች ሁሉ በቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው

- ✓ በቤተክርስቲያን ማንኛውንም መንፈሳዊ አገልግሎት ያለምንም እንቅፋት እንዲከናወን በትጋት ያገለግላሉ
- ✓ ቤተክርስቲያን ለምታከናውነው ልዩ ልዩ ስርዓቶች ( ቀብር የጌታ ራት ሰርግ ) በማስተባበርና በማገልገል አብይ ድረሻ የዲያቆናት ይሆናል
- ✓ በቤተክርስቲያን ለሚሰበሰበው አስራት በኩራት መባና ልዩ ስጦታ በዋናነት ያገለግላሉ የቤተክርስቲያኒቱ ገንዘብም ሆነ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት በትክክል እንድያዝ ድርጋሉ መያዙንም ያረጋግጣሉ
- ✓ ዲያቆናት የአገልግሎት ዘመን ልክ እንደ ሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን ይሆናል
- ✓ ዲያቆናት ቁጥራቸው በቤተክርስቲያኑ እድገት የሚወሰን ሲሆን የማዕድና የመስተንግዶ አገልግሎትን በስራቸው ያዋቅራሉ

- ✓ ዲያቆናት የራሳቸው ሰብሳቢና ጸሐፊ ሲኖራቸው የዲያቆናት ሰብሳቢ ሆኖ የሚመረጥ ሰው የመሪዎች ስብስብ አባል በመሆን በቤተክርስቲያን የመሪዎች አካል ይሆናል ፤፤

**የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች**

- የሙሉ ግዜ አገልጋዮች በመለኮታዊ ጥሪ በሙሉ ጊዜአቸው እንዲያገለግሉ ከጌታ ጥሪ የተቀበሉና ጥሪቸው በቤተክርስቲያን ታይቶ ፍሬአቸውም በብዙ ተፈትኖ ተቀበይነትን ያገኘ ከዚህም የተነሳ በጠቅላላ ጉባኤ ፊት እጅ በመጫን ስርዓት ተጸልዮላቸው የተሾሙ እረኞች ወንጌላውያን እንዲሁም ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን መታነጽ የሰጠውን በኤፌ 4፤11 ላይ በተጠቀሰው መሰረት አምና የምትቀበላቸውን ሐዋርያት ነብያት አስተማሪዎችን ጭምር ይሆናል ፤፤

- መለኮታዊ ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች ጥሪያቸውን ሚቀበሉት በቀጥታ ከጌታ ነው በመሆኑም ለዚህ ጥሪ ምላሽ ሲሰጡ ለሚያስፈላጋቸው ነገር ሙሉ በሙሉ በጠራቸው አምላክ በመታመንና በመደገፍ ነው ይሁን እንጂ መለኮታዊ ጥሪ ላላቸው አገልጋዮች ቤተክርስቲያን በኑሮአቸው ሊሚያስፈልጋቸው ትደግፋቸዋለች ፤፤
- ይህንንም ስታደርግ የገቢ ምንጭዋ ምዕመናኗ በገዛ ፈቃዳቸው ከሚለግሱት አስራት መባ እንዲሁም ልዩ ስጦታ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ጥሪ ያላቸውን አገልጋዮች የምታደርገው ድጋፍ አቅም እንደፈቀደ ይሆናል ፤፤ ይህም ማለት ለአገልግሎታቸው አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እና አገልግሎታቸውን ወደ ፊት ለማስሮጥ ይረዳ ዘንድ ነው፤፤ ይህም አገልጋዮች ከመንፈሳዊ አገልግሎታቸው በቀር ተጨማሪ የኑሮ ጫና እንዳይቀመጥባቸውና ለአገልግሎታቸውም እንቅፋት ላለማስቀመጥ ታስቦ ነው፤፤

**የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አቀባበል**

- ➢ ቤተክርስቲያን አንድ የሙሉ ግዜ አገልጋይን ለመቀበል መንፈስ ቅዱስ በግልጽ መልእክት ሲሰጣትና ጥሪ አለኝ የሚል /ትል/ አገልጋይ ሲቀርብ ሲሆን ጥሪውም በፍሬ በግልጽ በማያሻማ መልኩ ሲታወቅ ይሆናል ፤
- ➢ ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች ቤተክርስቲያኗን በመሪነት የሚያገለግሉ አገልጋዮች እጅ በመጫን ስርዓት በጠቅላላ ጉባኤ ፊት ጸሎት ከተደረገላቸው በኋላ የሙሉ ግዜ አገልግሎታቸውን ይጀምራሉ፤፤

**ሐዋርያት ፡** -

- ✓ ከጌታ መለኮታዊ ጥሪ ያላቸውና ለመጀመሪያ ግዜ ወንጌልን ላልሰሙ ሰዎች የክርስቶስን አዳኝነት በመስበክ ቤተክርስቲያንን የሚያንጹ ናቸው
- ✓ ለምትታነጸው ቤተክርስቲያን ፈር ቀዳጅና ጀማሪዎች ናቸው በመጨረሻም ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉ ሽማግሌዎችን መጋቢዎችንና በሌሎች የአገልግሎት ጸጋን የሚያገለግሉ አገልጋዮችን በመሾም በተወሰነ ስፍራ ቋሚ ሳይሆኑ የሚያገለግሉ ናቸው

**ነብያት** ፡- ለቤተክርስቲያን መታነጽ ላልዳኑት የእግዚአብሔር እጅ በህዝቡ መካከል እንዳለች ምስክር እንዲሆን በርቀት ሰለ ወደፊቱን እና በግዜ ስለ አሁን ለሚከሰተውም ነገር ከእግዚአብሔር መንፈስ ተቀብለው እና ሰምተው አቅጣጫ

በመስጠት ትንቢት በመናገር በቤተክርስቲያን ሙሉ ግዜያቸውን በመስጠት አልያም በትርፍ ግዜያቸው በቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው ።

**መጋቢዎች ፦** ጥሪዉን ከጌታ የተቀበለና በቤተክርስቲያን ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ በእረኝነት የሚያገለግል የመሪዎች ስብስብ ጉባኤ አባል በመሆን ቤተክርስቲያንን አባር ከሆኑ ሽማግሌዎች ጋር የሚመራም ጭምር ነው።

- ✓ አገልግሎቱ የየእለት የአማኝ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ስለሚመለከተው ትኩረቱም በቅድሚያ እዚሁ ላይ ይሆናል
- ✓ በቤተክርስቲያን እውቅና ላላቸው ስርዓቶች ሁሉ በዋናነት አገልግሎቱን ያከናውናል
- ✓ በቤተክርስቲያን ያሉትን የየአገልግሎት ክፍሎች በማደራጀት የየራሳቸው መሪ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ ዘርፉን በሰብሳቢነት ይመራል
- ✓ በቤተክርስቲያን ላሉ ምእመናንም ሆነ አገልጋዮች መንፈሳዊ እድገት እና ጤንነት በዋናነት ማገልገል


**አስተማሪዎች ፦** የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በመተርጎምና በማስተማር ጌታ ጸጋ የሰጣቸው ሙሉ ግዜያቸውን በመስጠትም ሆነ በትርፍ ጊዜ በቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮች ናቸው

- በልዩ ልዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርዕሶች ላይ መሰረታዊ ትምህርት ለአማኞች ይሰጣሉ በቤተክርስቲያንም ትምህርቶችን ያዘጋጃሉ
- አማኞች በስህተት ትምህርት እንዳይወሰዱ ያስተምራሉ የጌታ ጸጋ እንደረዳቸው በቤተክርስቲያን ለሚነሱ መጻፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች ከሌሎች አባር አገልጋዮች ጋር በመሆን መልስ ይሰጣሉ

**ወንጌላውያን ፦** የክርስቶስን አዳኝነት የሚናገሩ የምስራቹን ቃል ሁኔታዎች በሚፈጥሩላቸውና አጋጣሚውን ሁሉ በመጠቀም ወንጌልን ለማዳረስ ከጌታ ጥሪ ያላቸው ሆነው ሙሉ ግዜያቸውን በመስጠት የሚያገለግሉ አገልጋች ናቸው

- ➢ አዲስ ወደ ጌታ የመጡትን ተከታትለው በማስተማር ደቀመዝሙር ያደርጋሉ
- ➢ አማኞችን በቤተክርስቲያን ለወንግል ስርጭት ያነሳሳሉ በስራቸውም ያለውን የወንጌል ስርጭት የዘርፍ አገልግሎት በመምራት ያገለግላሉ ።

**CHURCH OPERATIONAL MINISTRY STRUCTURE**



**የአገልግሎት ክፍሎች ፡-**

- የአገልግሎት ክፍሎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ለአንድ ዓላማ ለእግዚአብሔር ክብር ለወንጌል መስፋፋትና ለአማኞች መታነጽ በልዩ ልዩ ጸጋና ክፍል የሚያገለግሉ እንደ የጸሎት ህብረት፤ የጋብቻ አማካሪዎች፤ የመዘምራን ህብረት፤ የሚድያ አገልግሎት፤ የወንጌል ስርጭት፤ የልጆች አገልግሎት፤ መስተንግዶ አገልግሎት፤ የረድኤት አገልግሎት ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን እያንዳንዱም የአገልግሎት ክፍል የየራሱ ዋና ሰብሳቢ እንዳስፈላጊነቱም ጸሀፊ ይኖሩታል፤፤
- የየአገልግሎት ክፍል ተጠሪዎች ወይም ሰብሳቢዎች ከቤተክርስቲያኗ መጋቢ ጋር በመመካከር ማንኛም ጥያቄም ሆነ ገንቢ ሐሳብ ለመሪዎች ስብስብ ያቀርባሉ ፤፤
- የአገልግሎት ክፍሎች ከየ ቡድን አጋሮቻቸው ጋር በሳምንት አሊያም በወሰኑት ቀን የራሳቸው የጸሎትን ስብሰባ ግዜ ይኖራቸዋል
- እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል የየራሱ የውስጥ መመሪያ ደንብ ከመሰረታዊው ዋና የቤተክርስቲያን መተዳደሪ ደንብ ጋር ባልተፋለሰ መልኩ ሲኖሩት ይህንንም በቤተክርስቲያን መጋቢ በኩል ለመሪዎች ስብስብ ያቀርባል ህህም ፋይል ሆኖ ይቀመጣል፤፤
- እያንዳንዱ የየአገልግሎት ክፍል ለአገልግሎት የሚረዳውን የገንዘብ ወጪ በተመለከተ የየሩብ ዓመት ወጪውን ለሂሳብ ክፍል በቤተክርስቲኒቷ አመታዊ በጀት መጀመሪያ ያቀርባል ፤ ምናልባት ከያዘው ኣመታዊ በጀት ተጨማሪ አገልግሎቱ ቢያስጠይቀው ጉዳዩ በወቅቱ በመሪዎች ስብስብ የሚወሰን ይሆናል

**የሒሳብ ሹም ፡-**

- የሂሳብ ሹም ተጠሪነቱ ለመሪዎች ስብስብ ሲሆን ይሆናል
- ያለውን ሂሳብ በህጋዊ መንገድ እንዲያዝ ከማድረጉም ሌላ በቤተክርስቲያን ያለውን ወጪ እና ገቢ ከህጋዊ ደረሰኝ ጋር በየሶስት ወሩ ለቤተክርስቲያኒቱ የዉስጥ ሂሳብ መርማሪ ወይም ኦዲተር አቅርቦ ያስመረምራል ውጤቱንም ለመሪዎች ስብስብ ያቀርባል፤፤
- የሂሳብ ሹም በቤተክርስቲን ለሚካሄደው ዓመታዊና የግማሽ ዓመት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ወጪና ገቢ ሪፖርት በግልጽ ያቀርባል ከአባላት ለሚጠየቀውም ማንኛውንም የሂሳብ ነክ ጥያቄዎች በአግባቡ ይመልሳል
- የአገልግሎት ዘመን ልክ እንደ ሽማግሌዎች ሁሉ በየሶስት ዓመት ሲሆን ዳግም ለአገልግሎቱ ከተፈለገ ለቀጣይ ሶስት ዓመት ያገለግላል ፤፤

## አጥቢያ ህብረቶች

- ይህ መተዳደሪያ ደንብ አጥቢያ ህብረት ብሎ የሚጠራቸው ምዕራብ ለንደን ባለችው በየህይወት እንጀራ ቤተክርስቲያን ስር በመሆን በለንደንም ሆነ ከለንደን ውጪ በየአከባቢ ያሉ ህበረቶችን ነው፤፤

- ❖ ህብረቶቹ ወደ አጥቢያነት እስኪያድጉ ድረስ በዋናዋ ቤተክርስቲያን ስር በመሆን ይተዳደራሉ ቤተክርስቲንም ህብረቶቹን ለማሳደግ አስፈላጊውን ሁሉ አቅሟእንደፈቀደ ታደርጋለች፤፤
- ❖ ህብረቶች የየራሳቸው መሪ እንደ ቁጥራቸው ያላቸው ሲሆን ለመምራት ብቁ የሆኑ መሪዎችና አገልጋዮች ሲኖራት በቤተክርስቲያኒቱ የውስጥ መመሪያ መሰረት ወደ አጥቢያነት ያድጋሉ

**የዕርምት / ዲስፕሊን/ እርምጃ**

- ➢ የእርምት እርምጃ የስነምግባር ጉድለት ያለበትን አንድን አማኝ ህይወቱን ለማቅናት ለማስተማር እንዲሁም ለማነጽ ሲሆን ለሌሎችም እንደ እግዚአብሔር ቃል መዳዝ ትምህርት እንዲሆን ታስቦ በቤተክርስቲያን የሚወሰድ ነው፤፤
- ➢ ግልጽ የሆነ ኃጢአት በተደጋጋሚ በሰራ ይህም በመረጃ የተረጋገጠና እንደ እግዚአብሔር ቃል ባልሆነ መንገድ በሚሄድ የቤተክርስቲያን አባልና ተባባሪ አባል ላይ የሚደረግ እርምት እርምጃ ነው ይህም ቤተክርስቲያን እንደ ሀጢአቱ ክብደት ከጉባኤ እስከ ማገድ ድረስ ልትደርስ ትችላለች ፤፤
- ➢ የእርምት እርምጃ ሂደት በማቴዎስ ወንጌል 18፤ 15- 17 እንደ እግዚአብሐር ቃል መሰረት ደረጃ በደረጃ የሚካሄድ ይሆናል
- ➢ በመጨረሻም አፈጻጸሙ በቤተክርስቲያን የውስጥ እርምት እርምጃ ሂደት ይሆናል፤፤

**ልዩ ልዩ መመሪያዎች**

**ሀ. የአገልግሎት ስንብት**

- ❖ አንድ አገልጋይ ከአገልግሎት የሚሰናበትባቸው መንገዶች ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን በራሱ ፍቃድ ሲለቅ
2. የቤተክርስቲያኗን መሰረተ እምነት የሚጎድ ትምህርት ሲያስተምር እና ይህም በእርምት እርምጃ ካልተመለሰ
3. ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ቃል የጣሰ ስነምግባር ግድፈት ሲገኝበትና በዚህም ምግባሩ የቤተክርስቲያን ስም ሲሰደብ
4. የቤተክርስቲያንን ህብረት እና አንድነት በስራውም ሆነ በአገልግሎቱ አደጋ ላይ እንደሚጥል ሲታመንበት ከአገልግሎት ይሰናበታል፤፤

**ለ. የስብሰባ ስርዓት፤-**

- ✓ መንኛውም የስብሰባ ስርዓት ባሉት የአባላት የድምጽ ብልጫ የሚወሰን ሲሆን ተመሳሳይ ድምጽ ከመጣ እንደገና ድምጽ እንዲሰጥ የሚደረግ ይሆናል ለሁለተኛ ግዚ ከሆነ ግን በእጣ ወይም በሰብሳቢው ውሳኔ የሚለይ ይሆናል
- ✓ ለውይይትና ለውሳኔ በሚጠሩ ስብሰባዎች ላይ ከአጠቃላይ ጉባኤው 2/3ኛው ሲገኝ ብቻ የሚከናወን ይሆናል ፤፤

**የመተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል**

- ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል እንዲለወጥ አሊያም ሊታረም የሚችል መሆኑን ቤተክርስቲያ ታምናለች

1. በቤተክርስቲያን መሪዎች እንዲሻሻል እንዲታረምና እንዲለወጥ ሲጠየቅ
2. በአገልግሎት ዘርፍ መሪዎች እንዲሻሻል እንዲታረምና እንዲለወጥ ሲጠየቅ
3. ከአባለት ጥያቄ ሲቀርብና ይህም በወቅቱ ባሉ የመሪዎች ስብስብ ሲታመንበት

**ደንቡ የሚጸናበት ግዜ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከላይ በተገለጸው የስብሰባ ስርዓት መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ የሚውል ይሆናል፤፤

*በዚህም ስርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእግዚአብሔር እስራኤልም ላይ ሰላምና ምህረት ይሁን (ገላ6፤ 16) አሜን፤፤*